# ቁማሩ ቀጠለ!



ታላቋን ኢትዮጵያ እንቅፋት መታና፣
አድርጓት አረፈ ቁማር መጫወቻ፡፡

ተንኮል ቁማርተኛው ካርታውን ፐወዘ፣
ተድሮውም ብሶ ቁማሩ ቀጠለ፡፡

ጆከርና ጦሩን እያቀያየረ፣
እንደተለመደው የመንጋ ራስ ላጨ፡፡

ጓሮዋ አራሽ አጥታ ሙጃ እንዳበቀለች፣
አገርም ሰው አጥሯት ቁማርተኛ ሾመች፡፡

ሽማግሌው ኤፍሬም ፓትሪያሪክ ማትያስ፣
ምኑ ያስደንቃል ቁማርተኛ ቢነግስ፡፡

ሲቆምር የሚውል የተንኮልን ቁማር፣
ምሁርና ሼኩ ጳጳሱ ሲከተል፣
ሁሉን የሚያይ አምላክ ሰማይ ሆኖ ምን ይል?

ከተንኮል ቆማሪ ተስፋ እየተበቀ፣
አማራ ትውልዱን ሕዝቡን አስጨረሰ፡፡

መንጋው ቁማርተኛን ቀበሮን ሲከተል፣
በተራ በተራ ሲለቀም ይውላል፡፡

ቁማር ተጫዋቹ ዓይኑን በጨው ታጥቦ፣
ተንኮል መቆመርያ ካርታውን ዘርግቶ፣
“እዚች ጋ ብትጥል ብልጥግና ዳቦ፣
እዚያ ብታስቀምጥ ጦቢያ ዓባይ ግድቡ፣”
ብሎ ሲያጫውተው መንጋውን ሰብስቦ፣

ከንፈሩን ይጥላል አይምሮ ዓይኑ ፈዞ፡ ፡

የንፁሐን አንገት ሆድን አሳርዶ፣
ክርስትያን አማራን ዘሩን አስበልቶ፣
በክህደት ወስከንባይ ደሙን ሽፍን አርጎ፣
ዛሬም እንደ ትናንት መንጋን አነሁሉሎ፣
ቁማሩን ቀጠለ ተበፊቱም ከፍቶ፡ ፡

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ነሐሴ ሁለት ሺ አስራ ሁለት ዓ.ም.